AMHARIC

ከታላቋ ማንቸስተር የህዝብ ጤና ቡድን
ለወላጆች እና ተንከባካቢዎች ጠቃሚ መረጃ

# ኩፍኝ



ኩፍኝ በዓለም ላይ ካሉ በጣም ተላላፊ በሽታዎች አንዱ ነው።
ይህ ማለት በቀላሉ ለመያዝ እና ለማሰራጨት ቀላል ነው።



ሰዎች በጣም ሊታመሙ አልፎ ተርፎም በሱ ሊሞቱ ይችላሉ።



በእርግዝና ግዜ ኩፍኝ ከተያዙ ልጅዎን ሊጎዳ ይችላል።



ነገር ግን እርስዎን ለመጠበቅ የሚያስችል አስተማማኝ ክትባት አለ።

ይህ በራሪ ወረቀት ስለዚህ ጉዳይ ይነግርዎታል።



## ኩፍኝ እንዴት ይሰራጫል?

አንድ ሰው በሚያስልበት ወይም በሚያስነጥስበት ግዜ በአየር ውስጥ ይሰራጫል።




## ምልክቶቹ ምንድን ናቸው?

ከፍተኛ ሙቀት እና የቆዳ ሽፍታ



## ኩፍኝ ምን ችግሮች ሊያስከትል ይችላል?

አዋቂዎች እና ህጻናት (ከ12 ወራት በታች) ከሌሎች ችግሮች ጋር የመጋለጥ እድላቸው ሰፊ ነው።



በአንዳንድ ሁኔታዎች ኩፍኝ የደረት ኢንፌክሽን፣ ራስን ስቶ መንፈራፈር፣ የአንጎል እብጠት እና የአንጎል ጉዳት ሊያስከትል ይችላል።



ልጆች ለ5 ቀናንት ያህል ሊተኙ እና ለ10 ቀናት ያህል ከትምህርት ሊቀሩ ይችላሉ።



## ክትባት

**ልጅዎን እንዲከተቡ በትምህርት ቤት ወይ ሐኪምዎ ይጠየቃሉ። በእባክዎን ፍቃድ ይስጡ።**



ክትባቱ ኤምኤምኣር (MMR) ይባላል።
ልጅዎን ከኩፍኝ፣ ጆሮ ደግፍ እና ሩበላ ይጠብቃል።



ለመከተብ በፍጹም በጣም አልዘገዩም።

ከፍተኛ የእድሜ ገደብ የለም።

ክትባታቸውን ያላሳደሱ/ያልወሰዱ አዋቂዎች ከጠቅላላ ሐኪማቸው ጋር ሊገናኙ ይችላሉ።

ምን ዓይነት የኤምኤምአር (MMR) ክትባቶች እንደወሰዱ እርግጠኛ ካልሆኑ፣ እባክዎን ስለእሱ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።

የእርስዎ ኤንኤችኤስ በዚህ ክትባት እና በኦቲዝም መካከል ምንም ግንኙነት እንደሌለ ይናገራል። በመላው ዓለም ያለስጋት ጥቅም ላይ ውሏል።



የጤና ቡድናችን ሊረዳዎት ይፈልጋል።
እባክዎን ያነጋግርዋቸው እና ማንኛውም ጥያቄ ይጠይቋቸው። ተጨማሪ በ www.nhs.uk/conditions/measles/ ያግኙ።